**ሳምንታዊ ዜና (ሐምሌ 5 ቀን 2000 ዓ. ም.)**

**ትምህርት ቤቶች በቀበሌና በወረዳ ካድሬዎች ዕዝ ስር ገቡ፣ አፋኝ የፕሬስ ሕጉን በመቃወም አለም አቀፍ ተቋማት መግለጫ እያወጡ ነው፣ «የባንዲራ ቀን» በሚል ወያኔ ያከበረውን በዓል የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ተቃወሙት፣ ግቢውን የፌዴራል ፖሊስ ወጥሮት ዋለ፣ የወያኔ መሪ ገመናዬ ለምን ወጣ በሚል የኦዲተር መስሪያ ቤቱን የሚመረምር አጣሪ ኮሚቴ የተባሉ ካድሬዎችን ሾመ፣ የአሶሳው ከንቲባ ወያኔን ከድተው በሱዳን ጥገኝነት ጠየቁ፣ የጅቡቲ ወደብ ታሪፍ ጭማሪ በሕዝቡ ላይ ከፍተኛ ጫና የሚፈጥር መሆኑ ተጋለጠ፣ እውቁና ዝነኛው ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሣሁን (ቴዲ አፍሮ) ለሐምሌ 14 ቀን 2000 ዓ.ም ተቀጠረ፣ በፍቼ ጦር ካምፕ ውስጥ የሰፈሩት ወታደሮችም ቴዲ ይፈታ ሲሉ ከፍተኛ ድምፅ አሰሙ »»»»**

**ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ ሌላም ዜና በዝርዝር ያንብቡ ..................................**

ግራ የተጋባው ወያኔ ትምህርት ቤቶችን በቀበሌና በወረዳ መስተዳድር ስር ማካተቱን ከትምህርት ሚኒስቴር ምንጮች የተገኘው ጥቆማ ገለፀ::

ትውልድ ገዳይ የሆነ ፖሊሲ ያወጣው ወያኔ ወጣቱን በቁጥጥር ስር ለማዋል ሲል ብቻ ትምህርት ቤቶች በቀበሌ ካድሬዎች ዕዝ ስር እንዲሆኑ መመሪያ ያስተላለፈ ሲሆን የትምህርት ሚኒስቴር ምን ሲሆን እንደሚችል ግራ መጋባታቸውን ምንጮች ገልፀዋል::

ወያኔ ወትሮም ለሀገርና ለሕዝብ፣ ለመጪው ተተኪ ትውልድ ፍፁም የማያስብ በመሆኑ ወደኋላ እንጂ ወደፊት የማያስኬድ የትምህርት ፖሊሲ አውጥቶ ከ10ኛ ክፍል ማጠቃለያ ብሔራዊ ፈተና እንዲሰጥ ካደረገ በኋላ በርካታዎች በየሰፈሩ ስራ አጥ ሆነው በመቅረታቸው የተነሳ እንደገና ወደ 12ኛ ክፍል ከፍ ያደረገ መሆኑን የገለፁት ምንጮች ባወጣው የትምህርት ፖሊሲ ትውልድ መቅጣቱ ሳያንሰው አሁን ደግሞ ትምህርት ቤቶች ሙሉ በሙሉ በቀበሌና በወረዳ አመራር ካድሬዎች ዕዝ ስር እንዲሆን መደረጉ ወያኔ የአፈና አገዛዙን አጠናክሮ መቀጠሉን ያሳያል ሲሉ ገልፀዋል::

ወያኔ ወጣቱን ትውልድ በፍርሀትና በችግር አሸማቅቆ በነፃነት ሀሳቡን መግለፅ እንዳይችል ለማድረግ አስቦ ገዳይ የትምህርት ፖሊስ ከማፅደቁም በተጨማሪ አስተዳደራዊም ሆነ ሌላ ግንኙነት ከቀበሌ ካድሬዎች ጋር እንዲሆን ትምህርት ቤቶችን የሚያስገድድ መመሪያ ማውጣቱ እጅግ የሚያሳዝን ከመሆኑም በላይ የአፈና ስርዓቱ በተጠናከረ መልኩ መቀጠሉን የሚያሳይ ነው ሲሉም ጨምረው ገልፀዋል:: አያይዘውም መምህሩ የፈለገውን አቋም እንዳያራምድ፣ ተማሪውም ብሶቱን እንዳይገልፅ ለማድረግ በትምህርት ቤቶች ውስጥ የተማሪዎችን መማክርት በሚል በደህንነት ስራ ላይ የተሰማሩ ተማሪዎችን የየዕለት እንቅስቃሴ የሚከታተሉና ሪፖርት የሚያቀርቡ ሲሆን አሁን ደግሞ ከትምህርት ሚኒስቴር ስልጣን ነጥቆ ለቀበሌ ካድሬዎች ስልጣን መስጠቱ የአፈና ስርዓቱ እጅግ መጠናከሩን የሚያረጋግጥ ነው ብለዋል::

በአሁን ሰዓት በገጠርም ሆነ በከተማ ያሉ መምህራን የወያኔ አባል እንዲሆኑ ግፊት እየተደረገ ሲሆን፣ ይህንን አላደርግም ባሉት ላይ የተለያዩ ጫናዎችን እየተደረጉባቸው እንደሚገኝም ለማወቅ ተችሏል::

ወያኔ መላው የሀገሪቷን ሕዝቦች በተለያየ መንገድ በየቀኑ ጫና እየፈጠረባቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ሀሳባቸውን በነፃነት እንዳይገልፁ፣ ችግሮቻቸውን በይፋ እንዳያወጡ አፋኝ የፕሬስ ሕግ ማፅደቁ ታውቋል::

የስልጣን እድሜውን ለማራዘም ሲል ብቻ ለዛሬ እንጂ ለነገ ፍፁም የማያውቀው የወያኔ ቡድን እራሱ ቀርፆ ያዘጋጀውን ሕገ መንግስት የሚፃረር የፕሬስ ሕግ አውጥቶ በተንቀሳቃሽ ሮቦቶች አማካኝነት ሰኔ 23 ቀን 2000 ዓ.ም ማፅደቁ እጅግ እያነጋገረ መሆኑ ታውቋል።

በሁሉም መንገድ የሕዝቡን የመናገር፣ የመፃፍና የመተንፈስ መብት ገድቦ ያለ አንዳች ችግር እቦርቃለሁ በሚል ሰሞኑን የአፋኝና ጨቋኝ የፕሬስ ሕግ ማውጣቱን በመቃወም በርካታ የአለም አቀፍ ተቋማት መግለጫ እያወጡ መሆኑ ታውቋል።

የወያኔው ቡድን ለሀገርና ለወገን ካለው ጥላቻና ንቀት የተነሳ ያሻውን እያደረገ በመሣሪያ ኃይል እያስፈራራ እንደልቡ ሲዘል የአለም ዲሞክራት ናቸው የሚባሉት እነ አሜሪካና እንግሊዝ ድርጊቱን እንዲገታ ከመምከርና ከመገሰፅ ይልቅ እንደ በኩር ልጃቸው እያዩ የገንዘብ እና የማቴሪያል ድጋፍ እያደረጉ መገኘታቸው አሣፋሪ ነው ያሉት አንድ ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህር በአሁን ወቅት በዚምባቡዌው መሪ በሮበርት ሙጋቤ ላይ እያደረጉ ያሉትን ጫና ሲሰውን እንኩዋን በነመለስ ዜናዊ ላይ አለማድረጋቸው የሚያሳፍርና የሚያበሳጭ ነው ሲሉም ይገልፃሉ።

ወያኔ ገና ለገና ገመናዬን ያጋልጡብኛል በሚል ብቻ የነፃ ፕሬስ ውጤቶችን በ1998 ዓ.ም ጥቅምት ወር ላይ ያገዳቸው ሲሆን፣ ከሁለት ያልበለጡ አዲስ ጋዜጦች ስራ ቢጀምሩም ሰሞኑን ባወጣው እጅግ በአለም የመጀመሪያ የሆነውን ገዳቢ፣ አፋኝና ጨቋኝ የፕሬስ ሕግ በማውጣቱ ስራቸውን ለማቆም እንደሚገደዱ ታውቋል።

በኢትዮጵያ ሕዝብ አቅም ያውም አንድ የነፃ ፕሬስ አሳታሚ ዝቅተኛ መቀጫ ተብሎ እስከ 100 ሺህ ብር ቅጣት መጣሉ እጅግ አስደንጋጭ ከመሆኑም በላይ የባለሥልጣናት ግድፈትና የስርዓቱን የቆሸሸ ገመና እንዳይወጣ ለማድረግ መሆኑን የገለፁት እኚሁ ምሁር በተለይም ለአቃቤ ሕግ የተሰጠው ገደብ የለሽ ስልጣን የሳንሱር ማድረግ ያህል ነው ሲሉ ገልፀዋል።

ዓቃቤ ሕግ የህትመት ውጤቱን ከጠረጠረና በወያኔ ላይ ምስጢር ያወጣል ብሎ ካመነ እንዳይታተም የመከልከል ስልጣን አለው ብሎ ማፅደቁ እጅግ አሳፋሪ ፍፁም በአለም ላይ የሌለ ግልፅ አፈና ነው ካሉ በኋላ የሚያሳዝነው አውጡ ሲባሉ እጃቸውን የሚሰቅሉ፣ አውርዱ ሲሏቸው እጃቸውን የሚያጣምሩት የወያኔ የፓርላማ አባሎች ይህንን የመሰለ ጦር የሰበቀና የሚዘነጠላቸው ሕገ ማፅደቃቸው የሚያሳዝን ማሰቢያ የሌላቸው የዕውቀት ደሀዎች መሆናቸውን በግልፅ ያሳየ ነው ብለዋል።

ሳይጠሯቸው አቤት ሳይልኩዋቸው ወዴት የሚሉት እነዚሁ የዕውቀት ድውዮች ለሆዳቸው እንጂ ለህሊናቸው የማይኖሩ ዛሬን እንጂ ነገን ፍፁም የማያውቁ ይህንን የመሰለ አንገት ቆራጭ ሕግ ማፅደቃቸውነገ በታሪክና በትውልድ ተጠያቂ መሆናቸውን ጠንቅቀው ሊያውቁት ይገባል ሲሉም አፅንኦት ሰጥተው ገልፀዋል።

የወያኔው ቡድን 17 ዓመታት የኢትዮጵያን ታሪክ ሲንድና ሲያበላሽ እንዳልነበር በአንድ ጀንበር ኢትዮጵያንና ሕዝቡዋን አፍቃሪ ለመምሰል የባንዲራ ቀን ብሎ ባከበረበት ወቅት ይፋ የሆነ ከፍተኛ ተቃውሞ ቀረበበት።

ቅዳሜ ሰኔ 28 ቀን 2000 ዓ.ም «የባንዲራ ቀን » በሚል የወያኔው ቡድን ከ10 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ አድርጐ ለ17 ዓመታትና ከዚያም በፊት በረሀ እያለ ታሪኩዋንና ባህሏን ሲንድና ሲያንኩዋሽሽ እንዳልነበር

ዛሬ የባለቤቱ ዋና ታሪክ ሰሪ ሆኖ ሕዝብ የጠላውን እንዲወደው እየተፍጨረጨረ ቢሆንም መላው የሀገሪቷ ህዝቦች በተለይም የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ አደባባይ ባለመውጣት የወያኔን ድግስ ባለማድመቅ ጥላቻውን በግልፅ ያሳየ ሲሆን የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎችም በግልፅ ተቃውሞ ሲያሰሙ ተስተውሏል።

በዚሁ እለት የሴቶች ማህበር፣ የፎረም ወጣቶች፣ የካድሬ ቤተሰቦችና ካድሬዎች ተሰባስበው «የባንዲራ ቀን» በዓል በሚል የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊና ጓሌዎቹ ጨርቅ ነው እያሉ ሲያጣጥሉት እንዳልነበረ ባንዲራውን የፈጠሩት እነሱ እራሳቸው ለማስመሰል በአዲስ አበባ ስታዲየም በዝግ ሲያከብሩ የታየ ሲሆን እንደ ፎረም ወጣት ማህበር ሁሉ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን ይህንኑ አላማ ደግፈው ወደ ስታዲየም እንዲወጡ ሲጠየቁ ወትሮም ውስጣቸው እረመጥተቀጣጥሎ የነበረው ተማሪዎቹ በአንድነት ዘር ኃይማኖት ሳይለዩ ከፍተኛ ተቃውሞ አሰምተዋል።

ልኩን ያላወቀው ወያኔ ተኝቶ የነበረውን የተማሪዎች እንቅስቃሴ በመቀስቀሱ «የባንዲራ ቀን» በሚል የሚያከብረውን በዓል ሊያበላሹበት መሆኑን በመረዳቱ ግዙፍ የፌዴራል ሠራዊት በዩኒቨርስቲው ዙሪያ ከማስፈሩም በተጨማሪ ወደ አደባባይ ወጥተን ተቃውሟችንን እናሰማለን በማለታቸው በበሩ አካባቢ ተሰብስበው በነበሩ የዩኒቨርስቲው ተማሪዎች ላይ አስለቃሽ ጥይት በመተኮስ ከአካባቢው ወደ ውስጥ የመለሷቸው መሆኑንም በስፍራው የተገኙት የአይን እማኞች ገልፀዋል።

ወያኔ ተማሪውን በረሀብ እየቆላ በቀን ሁለት ብጣቂ ዳቦና ከውሃ የቀጠነ ሽሮ ጋር እየሰጠ ባለበትና ተማሪው በራሱና በሀገሪቷ ሕዝቦች ላይ በሚደርሰው ችግር የተነሳ ከፍተኛ ቁጣ በውስጡ ሲንቀለቀል ባለበት ወቅት የወያኔ አርማ ያለበት ሰንደቅ አላማ ለተማሪዎቹ አድሎ በሰልፍ ወጥተው እንዲደግፉት የሞከረ ቢሆንም ተማሪዎቹ ከፍተኛ ተቃውሞ ያሰሙ ከመሆኑም በላይ «ታሪክ በራኸና ከላሽ፣ የኢትዮጵያ ባንዲራን ያዋረደ . . .» በሚል ሲቃወሙ ተደምጠዋል።

የኢትዮጵያ ታሪክ ከ100 አይበልጥም እያለ ሲለፍፉ እና በየሄዱበት ቱልቱላቸውን ሲነፉ የነበሩት የወያኔ መሰሪ ባለሥልጣናት ሕዝቡ ጥላቻውን በግልፅ ባስቀመጠበት ወቅት ድጋፍ አገኛለሁ በሚል ብቻ ባንዲራን የፈጠሩት እነሱ መሆናቸውን ለማስመሰል «የባንዲራ ቀን » በሚል እንደ ግሪሳ ወፍ ተሰባስበው ለማክበር በተዘጋጁበት ወቅት በአዲስ አበባ ተማሪዎች ከፍተኛ ተቃውሞ ሲሰማ እንደነበረ ታውቋል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ዙሪያ የአድማ መበተኛው የፌዴራል ፖሊስ መኪናዎች ሶስት ያህሉ በዋና ዋና በሮች በኩል ተደብቀው ቆመው እንደነበረ የጠቆሙት የአይን እማኞች ግቢው መትረየስ ተጠምዶ ዙሪያውን በፌዴራል ፖሊስ ሲጠበቅ እንደዋለ ገልፀዋል።

ይህ ሁሉ ድርጊት ሲፈፀምና በተለይ ሕዝብ እንዳልደገፋቸው የሚያውቁት የአሜሪካ ኤምባሲ ዲፕሎማቶች አንዴ ወደ ላይ ሌላ ግዜ ወደታች እየተመላለሱ በካሜራ የተማሪዎቹን እንቅስቃሴ ሲቀርፁ እንደነበረ የገለፁት የአይን እማኞች ወያኔ በሌለው ታሪክና ሞራል የኢትዮጵያን ባንዲራ ለማክበር መሯሯጡም ያሳፍራል ሲሉ ተማሪዎቹ ግልፅ ተቃውሞ ሲያሰሙ ተደምጠዋል።

የሕዝቡን ባህል እና ወግ የሀገሪቷን ክብርና ዝና አዋርዶ ሰድቦ ለሰዳቢ የሰጠው ወያኔ ያለ አንዳች ይሉኝታና ሀፍረት እራሱ የታሪክ ባለቤት ለመምሰል የባንዲራ ቀን በሚል ያከበረ ሲሆን፣ በዕለቱ የቃለ ምህላ ፕሮግራም አከናውኗል፡

እስከ ዛሬ የኢትዮጵያ ባንዲራ እንዳልነበረና ከሰኔ 28 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ አምነው ለመቀበል የተገደዱት ወያኔዎች አዛውንቱ ግርማ ወልደጊዮርጊስን ጨምሮ እስከ ታች ካድሬ ድረስ የእጃቸውን መዳፍ ወደ ላይ በመዘርጋት ቃለ ምህላ የፈፀሙ መሆኑን የተከታተሉ የሀገሪቱ ሕዝቦች እስከ እስከ ዛሬ በፈፀሙት ድርጊት ሲናደዱ እንዳልነበረ ዛሬ መልሰው መሀላ መፈፀማቸው የሚገርምና የሚደንቅ ታሪክ ነው ብለዋል፡፡

የአንድ ሀገር መሪ ነኝ በሚል ስልጣን ላይ ተጉልተው የነበሩት እነ ወያኔ 17 ዓመታት ተቀምጠው ዛሬ መሀላ መፈፀማቸው የሚያሳዝን ነው ያሉት አንድ አባት አርበኛ ታሪክ ግን ምንጊዜም ፍርድ የሚሰጥ በመሆኑ ተገድደው ይህንን ቀን ሊያከብሩም የኢትዮጵያ ባንዲራ ጨርቅ ነው እያሉ ሲያዋርዱ እንዳልነበረ እነሱ ተዋርደው ጨርቅ ነው ያሉት ባንዲራ ተከብሮ መዋሉ የሚያስገርም ነው ብለዋል፡፡.

ተቃውሞውን በመቀጠል ሰኞ ሰኔ 30 ቀን 2000 ዓ.ም በአብዛኛው የ6 ኪሎ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ወደ ክፍል ባለመግባታቸው የተነሳ ትምህርት ሳይካሄድ እንደቀረም ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ወያኔና ባለሥልጣናቱ «የባንዲራ ቀን» በሚል በስታዲየም ውስጥ ባከበሩበት ወቅት የራሳቸው የምክር ቤት አባሎች በዓሉን በመተው የውሎ አበል በሚከፈላቸው የኤድስ ትምህርት ላይ እንደዋሉ የምክር ቤቱ ምንጮች ገለፁ፡፡

ከ100 ብር በታች የውሎ አበል የተከፈላቸው የወያኔ የምክር ቤት አባሎች ለበዓሉ ያላቸውን ንቀት በመግለፅ በኤድስ ትምህርት ላይ እንደዋሉ የገለፁት ምንጮች በነበረው እንቅስቃሴ ድብቅ ተቃውሞ ሲያሰሙ እንደነበረም ምንጮቹ ጠቁመዋል፡፡

ሰኔ 30 ቀን 2000 ዓ.ም ምክር ቤቱ ስራውን አጠናቀቀ ተብሎ ከመዘጋቱ በፊት የደኞችን ሹመት ያፀደቀ ሲሆን፣ የወያኔን ገመና ያጋለጠው የዋናው ኦዲተር መስሪያ ቤት ሪፖርት የሚመረምሩ የወያኔ ካድሬ ጀሌዎቹ የተሾሙ መሆኑን ከምንጮቹ ገለፃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በሚያምነውና ቀኝ እጅ ነው የሚባለው ስዩም መስፍን የሚመራው ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብዙ ገንዘብ እንደተመዘበረም በባለሥልጣናቱ ትዕዛዝ ከብሔራዊ ባንክ በብድር 3 ቢለዮን ብር በላይ ወጪ ተደርጐ መወሰዱና ከዚሁ ጋር በተያያዘ በሀገሪቱ ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት ተፈጥሯል በማለት ደፍረው ሪፖርት ባቀረቡት የኦዲተር መ/ቤት ሰራተኞች ላይ እርምጃ ለመውሰድ እንዲያመች ካድሬዎች መሾሙ ታውቋል፡፡

የወያኔ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ስርዓቱን እየከዱ ወደ ውጭ ሀገር መኮብለላቸውን አሁንም እንደቀጠሉበት ታወቀ፡፡

ሰሞኑን የአሶሳ ከተማ ከንቲባና የወያኔ ሹመኛ ካድሬ ወደ ሱዳን ኮብልሎ ጥገኝነት መጠየቁን የገለፁት ምንጮች ይህንኑ ተከትሎ በሱዳን ወታደሮችና በወያኔ ጦር መካከል መጠነኛ ግጭት መቀስቀሱን ገልፀዋል፡፡

እንደ መከላከያ ውስጥ አዊቂ ምንጮች ገለፃ ከሆነ የአሶሳው ከንቲባ አህመድ ከሊፋ ወደ ሱዳን ውስጥ ገብቶ ካርቱም ጥገኝነት መጠየቁን እና በአሁን ሰዓት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በኩል የመልስሉኝ ጉዳይ ላይ እየተነጋገሩ እንዳሉም ገልፀዋል።

የመረጃና ደህንነት ግብረ ኃይል ተብሎ የተቋቋመው የወያኔ ቡድን እራሱ የሚያዘውና ተወርዋሪ አድርጎ የሚልከው ኃይል ያለው ሲሆን፣ ግለሰቡ በከዳ ወቅት ሪፖርት እንደደረሳቸው በድንበር አካባቢ ሰፍሮ የሚገኘ ው የሜጀር ጄኔራል ስዩም ሐጉስ የሚያዘው ጦር በመኖሩ ይህንኑ ኃይል እንዲንቀሳቀስ ተደረገ እንጂ ከሱዳን ጋር ፍፁም ግጭት ለመፍጠር ያልተደረገ መሆኑን የገለፁት ምንጮች በጐደንርና በአርማጭሆ በመተማ ለም መሬት ቆርሶ የሰጠው ወያኔ ከሱዳን ጋር ሊጋጭ አይችልም ሲሉ አፅንኦት ሰጥተው ገልፀዋል።
ይህንንም ሲያብራሩ የኢትዮጵያን ለም መሬት የተሰጠው የሱዳን መንግስት በሱዳን ድንበር ላይ ሆነው ወያኔን የሚያጠቁ የታጣቂ ኃይሎችን ከግዛቱ እንዳያባርርለት የተስማሙ በመሆኑ ከዚህም በተለይ በጋምቤላ በኩል ይህንኑ ግዳጁን እየተወጣ ሲሆን፣ በጐንደርም ቢሆን ሙከራ እያደረገ እንደሚገኝ ምንጮች ገልፀዋል።

ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ ግዛት የነበረው በጋምቤላና በጐንደር በኩል ተቆርሶ ለሱዳን የተሰጠውን መሬት እንደ እጅ መንሻ የተጠቀመበት ወያኔ ከዚህም ሌላ በተጨማሪ የገንዘብና የነዳጅ ድጋፍ ስለሚያገኝ የሱዳንን እጅ ከመመልከት ባለፈ ሌላ ታሪክ ሊፈፅም እንደማይችልም የተረጋገጠ ሲሆን፣ ግርግሩን ተጠቅሞ ሕዝቡን ለማሳሳት የተደረገ ነው ሲሉም ገልፀዋል።

በቅርቡ የመተማንና የታች አርማጭሆ መሬት መቆረስ ተከትሎ በአካባቢው ይንቀሳቀሳል የተባለው የአትዮጵያ ታጣቂ ተቃዋሚ ኃይል በወያኔ ጦር ላይ ጉዳት አድርሶ ከፍተኛ ኪሳራ ውስጥ ከትቶት እንደነበረ ምንጮቹ አስታውሰው በአሁን ሰዓትም በአካባቢው ውጥረት ነግሶ እንደሚገኝም ገልፀዋል።

ወደ ሱማልያ ውስጥ ታህሳስ 1999 ዓ.ም ጦሩን ይዞ የገባው ሜጀር ጄኔራል ስዩም ሐጐስ በጥቂት ቀናት ውስጥ በርካታ ወታደሮችን ያስጨረሰ ለዚህም ውለታው ከብርጋዴየር ጄኔራልነት ወደ ሜጀር ጄኔራልነት ከፍ ያለ መኮንን ሲሆን፣ አሁንም በጐንደር በኩል ታጣቂዎች በሚሰነዝሩት ድንገተኛ ጥቃት የተነሳ በሚመራው ጦር ላይ ከፍተኛ ኪሳራ እየደረሰበት በመሆኑ ስሙን ለማደስ የኮበለለውን የአሶሳ ከተማ ከንቲባ ለመያዝ ሙከራ ቢያደርግም ሳይሳካለት መቅረቱንና በዚህም ግጭት መፈጠሩን መንጮቹ አጋልጠዋል።

የአፍሪካ የመሪዎች ጉባኤ በአዲስ አበባ ሊደረግ ታቅዶ በዚሁ ጉባኤ ላይ ለመገኘት መጥቶ የነበረው የግብፁ መሪ ሆስኒ ሙባረክ ቦሌ አካባቢ ሲደርስ የግድያ ሙከራ ተደርጐበት እንደነበርና አንደኛው ተጠርጣሪ ሱዳን በመግባቱ የተነሳ የወያኔና የሱዳን ግንኙነት ሻክሮ የነበረ ቢሆንም በአሁን ሰዓት ግን አፈር አይንካህ እየተባባሉ እየተወዳደሱ የሚገኙ በመሆናቸው ይህ የሚባለው ግጭት ሆን ተብሎ የተከሰተ ነው ብሎ ለማለት ይከብዳል የሚሉ ዲፕሎማቶችም በርካቶች ናቸው።

በአሁኑ ሰዓት ሱዳን ለኢትዮጵያ ታጣቂ ኃይሎች አንዳችም እርዳታና ድጋፍ አታደርግም ያሉት ለዲፕሎማቲክ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ይህንን የምታደርግ ከሆነ ወያኔም የዳርፉር አማፅያንን ድጋፍ ሰጥቶ የአልበሽርን መንግስት ሊያናጋው ይችላል ስለዚህ ሁለቱም እሾህን በእሾህ እንዲሉ ወዳጅነት ላይ ጠንክረው እየሰሩ ናቸው ብለዋል።

ምንም እንኳዋን የሱዳን መሪ የወያኔ ጦር በሱማሌ መግባቱን ቢቃወምም ከወያኔ ጀርባ ያሉት እነ አሜሪካን በመሆናቸውና የዳርፉር አማፅያን ችግር ያለበት በመሆኑ ዝምታን መርጠው እንዳሉ የጠቆሙት ለዲፕሎማቲክ ቅርበት ያላቸው ወገኖች አሁን ባለው ሁኔታ ሁለቱም ጋር ይፋ የሆነ ግጭት አልተፈጠረም ሲሉ ገልፀዋል።

በሌላ ዜና የወያኔ መጠቀሚያ የሆነው የጅቡቲ ወደብ ከፍተኛ ጭማሪ ማድረጉ ታወቀ። ሰሞኑን ጭማሪውን ይፋ ያደረገው የጅቡቲ መንግስት የራሴ ናቸው ያላቸው የኑሮ ውድነትና የመሳሰሉትን ምክንያቶች በመደርደር የገለፀ ቢሆንም የወደቡ ታሪፍ ጭማሪው ተገቢ አይደለም ከማለት ባለፈ ሌላ ምንም ማድረግ የማይችለው ወያኔ ታሪፉን መልሶ ወደ ሕዝቡ ላይ ሊጭን እንደተዘጋጀ የንግድና ኢንዱስትሪ መስሪያ ቤት ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፁ።

በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ በረሀብ ማዕበል ውስጥ ባለች ሀገርና በአለም ላይ እጅግ ከፍተኛ የኑሮ ውድነት አለባት በተባለችው በዚህችው ሀገር ላይ የወደብ ታሪፍ ጭማሪ መደረጉ ከድጡ ወደ ማጡ መሆኑን የገለፁት ምንጮች ወያኔ አስቀድሞ አጨብጭቦና እየዘለለ አስረክበ ወደብ አልባ አድርጓት ያለ በመሆኑ የተባለውን ሁሉ አሜን ብሎ መቀበል ብቻ አማራጩ ነው ያሉት ምንጮች ይህንን ማድረግ ካልቻለ ሌላ ምንም የሚወስደው እርምጃ የሌለው ሲሆን፣ ሕዝቡ ግን እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታ ሊገጥመው እንደሚችል ከወዲሁ ስጋት ማሳደሩንም ጨምረው ገልፀዋል።

ቀድሞ ከነበረው በተጨማሪ አዲሱ የወደብ ታሪፍ ሲመጣ በአመት 220 ሚሊዮን ብር ጭማሪ ያስየ መሆኑም ታውቋል።

በመጨረሻም ከ3 ወር በፊት በሀሰተኛና በፈጠራ ክስ ተመስርቶበት ወህኒ የወረደው እውቁ ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ ለመጨረሻ ብይን ተብሎ ሐምሌ 4 ቀን 2000 ዓ.ም የተቀጠረ ቢሆንም ውሣኔ ሳያገኝ አሁንም ለሐምሌ 14 ቀን 2000 ዓ.ም ለሌላ ተለዋጭ ቀጠሮ ተቀጠረ።

ሰኔ 27 ቀን 2000 ዓ.ም ብይን ይሰጣል ተብሎ ተቀጥሮ የነበረ ቢሆንም ዓቃቤ ሕግ የተምታታ ማስረጃ አቅርቧል በሚል ለሐምሌ 4 ቀን 2000 ዓ.ም የተቀጠረ ቢሆንም በዚህም ዕለት ብይን ሳይሰጥ ለሌላ ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጥቷል።

ሐምሌ 4 ቀን 2000 ዓ.ም ውሣኔ ያልተሰጠበት ምክንያት የዳግማዊ ምኒልክ የአስክሬን ምራመራ ባለሙያ ቀርቦ ስለተሳሳተው የቀን ቁጥር እንዲያስረዱ ትዕዛዝ በመስጠቱ በዚያው ሆስፒታል የሚሰሩት የኩባው ሀኪም ቀርበው በስፓኒሽኛ እየተናገሩ በአስተንሚ በል የተባሉትን የተናገሩ ሲሆን ይህንንም አይቶ ለመበየን ቀጠሮ የተሰጠ መሆኑ ታውቋል።

ዓቃቤ ሕግ ከዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል አገኘሁት ብሎ ያቀረበው ማስረጃ ሚች ደጉ ይበልጣል የተባለው በ22/2/99 ዓ.ም አስክሬኑ ገብቶ በማግስቱ በ23/2/99 ዓ.ም ተመርምሮ ወጥቷል ተብሎ በእንግሊዝኛ የተፃፈ ሲሆን የቴዲ አፍሮ ጠበቃ ግን የቀረበው ማስረጃ ተከሳሹን ፍፁም የማይመለከተው በመሆኑና በቴዲ ላይ የቀረበው ክስ በ23/02/99 ዓ.ም ከሌሊቱ 8 ሰዓት ው ገጭቶ አምልጧል የሚል በመሆኑ ከድርጊቱ ጋር የማይገናኝ በመሆኑ ውድቅ ተደርጎ በነፃ ሊሰናበት ይገባል ቢሉም የወያኔ ካድሬው ዳኛ ልዑል ገ/ማሪያም ግን አይደረግም ዓቃቤ ሕግ የተሳሳተውን ማስረጃ አስተካክለህ እንድትመጣ ብሎ በማዘዙ ቀኑን አስተካክለው ያመጡ

ከመሆኑም በላይ የአስክሬን ሀኪም ነው የተባለውን ኩባዊ ለምነውና አግባብተው በዚህ ዙሪያ ማብራሪያ እንዲሰጥላቸው አድርገዋል።

በዚህም መሠረት ኩባዊው ሀኪም ቀን የተሳሳተው ከዋናው መዝገብ ላይ ከመገልበጥ የመጣ ስህተትነው ስለዚህ ይቅርታ በማለት በል የተባለውን ሁሉ ገልፀዋል። ጠበቃውም መስቀለኛ ጥያቄ ሲጠይቁት የተደናገጠውና ምላሽ ያጠረው ሲሆን፣ ዳኛ ልዑል ገ/ማሪያም ግን ይህ የምስክሩን መብት መጋፋት በመሆኑ ጥያቄው ውድቅ ነው እያለ እራሱ ከሳሽ፣ እራሱ መስካሪና እራሱ ዳኛ ሆኖ መዋሉ አስገራሚ ነበር።

በመሆኑም ይህንን የኩባውን ሐኪም ካደመጠ በኋላ ለመጨረሻ ግዜ ብይን ለመስጠት ሐምሌ 14 ቀን 2000 ዓ.ም እንደተወሰነ ታውቋል።

በዕለቱ በነበረው የአቃቤ ሕጉና ዳኛው ትዕይንት የተበሳጨው ቴዲ አፍሮ እጁን አውጥቶ የመናገር ዕድል እንዲሰጠው ጠይቆ « የሰውን ልብና ስሜት የሚመረምረው እግዚአብሔር ነው። ሕዝብ እንዲያውቅልኝ የምፈልገው ነገር እኔ ሰው አልገጨሁም፣ አልገደልኩም። በሀሰተኛ ክስ ለሶስት ወራት ታስሬ ተባይ እየበላኝ እገኛለሁ። የሚመለከታቸው የበላይ አካላት ጣልቃ ይግቡበት እኔ ባልሰራሁት ወንጀል እየተንገላታሁ ነው» በማለት ሀሳቡን ሲገልፅ በችሎቱ የነበሩት በሙሉ በእንባ ሲራጩ ታይተዋል።

ዳኛ ልዑል ገ/ማሪያም ፍርዱን አንተታችሁብን እያልከን ነው። እኛ ብዙ ፋይል አለብን ብዙ ስራዎችም አሉን። በማለት የለበጣ ሳቅ እየሳቀ መልስ ሰጥቷል።

ከወትሮው በተለየ መልኩ ግቢውን ያጣበበው የሕዝብ ብዛት ያስደነገጣቸው የፌዴራል ፖሊሶች በስውር ጥበቃና በመትረየስ የፍርድ ቤቱን ዙሪያውን ጥበቃ ሲያደርጉ እንደነበር ታይቷል።

በተያያዘ የባንዲራ ቀን ተብሎ በተለያዩ ከተሞች ከፍተኛ ገንዘብ ወጪ አድርጎ ወያኔ እያከበረ ሲሆን፣ ሰኔ 29 ቀን 2000 ዓ.ም በፍቼ ጦር ካምፕ ውስጥ ያሉት ወታደሮች እንዲያከብሩ ታዝዘው ወደ ከተማ የገቡ ቢሆንም በዕለቱ ወታደሮቹ «ቴዲ ይፈታ! ቴዲ ይፈታ! . . .» እያሉ በከፍተኛ ድምፅ ሲያሰሙ እንደዋሉ ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልጿል።

ወታደሮቹ ተወርዋሪ ኃይል ናቸው ተብለው ከየጦሩ ክፍል ተመርጠው የመጡ ሲሆን የባንዲራ ቀን ተብሎ እንዲያከብሩ ቢታዘዙም መፈክራቸው ቴዲ ይፈታ የሚል ሆኖ መዋሉ እጅግ አስገራሚ እንደነበር ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል። በወቅቱ ወታደሮቹ ይህንን መፈክር ሲያሰሙ ያደመጡት አለቆቻቸው በመደናገጥ እርምጃ እንወስድባችኋለን እያሉ ሲያስፈራሯቸው እንደነበረም ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሏል።

<u>**ዜና ማስታወሻ**</u>

- በሀገሪቱ ነዳጅ በመጥፋቱ የክፍለ ሀገር አውቶቡሶች ስራ አቆሙ፤
- አዲስ አበባ መነኻሪያ ያሳፈሩትን መንገደኛ ገንዘብ እየመለሱ አስረዱዋቸው፤

- ከዛሬ ሐምሌ 5ቀን 2000 ዓ. ም.ጀምሮ በሀገሪቱ ያሉ ነዳጅ ማደያዎች 10 ሺህሊትር ናፍጣ መጠባበቂያ እንዲይዙ ትዕዛዝ ተሰጠ፤

- ባለስልጣናቱ ነዳጅ እጥረቱ የተፈጠረው ከውጭ ጭና የምትመጣው መርከብ ስለዘገየች ነው እንጅ እጥረት ተፈጥሮ አይደለም እያሉ አይን ያወጣ ውሸት ይዋሻሉ፤

- ለሁለት ቀናት በመላ ሀገሪቱ የኢንተርኔት አገልግሎት ተቋዋርጦ ነበር፤

- በርሀቡ ፤በኑሮ ውድነቱ እና በመሳሰሉት መልዕክት እንዳይተላለፍ ለማድረግ ታስቦ መሆኑ ታውቋዋል፤

- ደህንነቶችም ኢንተርኔት ተጠቃሚ መስለው የስለላ ስራቸውን ዕያከናወኑ መሆኑ ታወቀ፤